# ወያኔ/ኢሕአዴግ የሱዳን ወኪል ሁኖ በወገኖቻችን ላይ ጥቃት አደረሰ ፤ እስረኞች በሕዝብ ትግል ተፈቱ

**ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ**
**የተሰጠ መግለጫ**

**ግንቦት** 30 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( June 7, 2008 )

**በጎንደር ክፍለ ሀገር በታች አርማጭሆ ወረዳ የሚገኙት ጀግና ወገኖቻችን በሱዳን የታሰሩትን ወገኖቻችንን ለማስፈታት በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ፤ እንዲሁም በውጭ ሀገሮች የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ወያኔ/ኢሕአዴግና የሱዳን መንግሥት ድንበራችንን አስመልክተው የሚፈጽሙትን ደባና ተንኮል በተመለከተ ለዓለም ህብረተሰብ በማስረዳትና በማሳወቅ ባካሄድነው ከፍተኛ የዲፕሎማሳዊ ትግልና የማጋለጥ ዘመቻ የተነሳ በወያኔ/ኢሕአዴግና በሱዳን ላይ ከፍተኛ ጫና በማሳደራችን በሱዳን እስር ቤት ሲማቅቁ የነበሩትን** 26 **ወገኖቻችንን ግንቦት** 29 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( June 6, 2008 ) **ለማስፈታት ተችሏል። ዝርዝር ሁኔታው እንደሚከተለው ነው ፥**

## የሕዝብ ተቃውሞ ፥

**ከጥቂት ቀናት በፊት በጎንደር ክፍለ ሀገር የሚገኘው የአርማጭሆና የቋራ ሕዝብ በሱዳን የታሰሩትን ኢትዮጵያውያን እስረኞችን ለማስፈታት በወሰደው የተጠናከረ ቆራጥ እርምጃ ወደ ሱዳን ዘልቆ በመግባት በሱዳን ሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ( በሱዳን አጠራር ሎሪ የሚባለው ) ይዞዙ የነበሩ ሱዳናዉያን በሙሉ አስገድዶ ወደ ኢትዮጵያ በማምጣትና ሰዋራ ቦታ ካስቀመጠ በኋላ ፤ በሱዳን የታሰሩ ወገኖቻችን እስካለቀቁ ድረስ ሱዳናውያኑን እንደማይፈቱ ለአካበቢው የሱዳን መንግሥት ባለሥልጣናት አሳውቀው ነበር። ይህም እርምጃ በሱዳን መንግሥትና በወያኔ /ኢሕአዴግ ላይ መደናገጥና መሸበርን ፈጠረ።**

**ለወገኖቹ ፣ ለሀገሩ ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ደንታ የሌለው ፣ አንድም ኢትዮጵያዊ የተፈናቀለ ፤ አንድም ኢትዮጵያዊ በሱዳን የታሰረ የለም ብሎ በገሃድ በአደባባይ ነጭ ውሸት የዘራው የከሃዲው መለስ ዜናዊ አገዛዝ የሱዳን ወኪል በመሆን በአካባቢው ሕዝብ የታገቱትን ሱዳናውያንን በኃይል ለማስፈታት በከባድ መሳሪያና በሄሊኮፕተሮች የታገዘ ጦር ወደ አብደራፊ አካባቢ አሰማራ።**

**ግንቦት** 28 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( June 5, 2008 ) **በአካባቢው ሕዝብና በወያኔ/ኢሕአዴግ ጦር መካከል አብደራፊ አካባቢ ለረጅም ሰዓት በተካሄደው ከፍተኛ ጦርነት ከ**20 **በላይ የወያኔ ወታደሮች ተገድለዋል። በዚህ ውጊያ ላይ የአካባቢው ሚሊሻ አዛዥ የነበረው ሻምበል ቻሌ አለሙ የተገደሉ ሲሆን ፤ የቀብር ሥነ- ሥርዓታቸው ቅዳሜ ግንቦት** 30 **ቀን** 2000 **ዓ.ም.** ( June 7, 2008 ) **በጎንደር ከተማ ተፈጽሟል።የታገቱትን ሱዳናውያን የወያኔ/ኢሕአዴግ ጦር በኃይል ሊያስፈታ ችሏል።**

## የእስረኞች ጉዳይ ፥

ከዚህ ቀደም ሲል በሱዳን ወታደሮች ታፍነው ተወስደው ስንጃ ከተማ ታስረው ከነበሩት 28 እሰረኞች መካከል ፤ ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. ( June 4, 2008 ) 2 ተፈተዋል። እነርሱም ፥

1ኛ/ አቶ አብዱ አይደር ( ነብስ ገበያ ላይ የነበረው የእርሻ ጣቢያ ሹፌር ) የተፈረደባቸውን 1 ሚሊዮን የሱዳን ፓውንድ ለመክፈል ዋስ ጠርተው ተለቀው ወደ ሱዳን ርዕሰ ከተማ ካርቱም ሲሄዱ ፤

2ኛ/ አቶ መሐሪ መብራህቱ ( የእርሻ ጣቢያ ባለንብረት ) ደግሞ የተፈረደባቸውን 2 ሚሊዮን የሱዳን ፓውንድ ከፍለው ከተለቀቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመተማ በኩል አልፈው ሽህዲ ከተባለው ትንሽ ከተማ እንደገቡ ተረጋግጧል።

ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ( June 6, 2008 ) በሱዳን ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት በኋላ 3:00PM ስንጃ ከተማ እስር ቤት የሚገኙት 26 እስረኞች በ 3 የሱዳን ጦር ሰራዊት መኪናዎች ሆነው ወደ ሱዳን ከተማ ጋላባት ( ከመተማ ማዶ ያለ ከተማ ) ተወስደዋል። ወገኖቻችን ወደ ጋላባት ሲሄዱ ከካርቱም የመጡ 2 የኢትዮጵያ ኢምባሲ ባለሥልጣናት ተገኝተው ነበር።

ዛሬ ግንቦት 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ( June 7, 2008 ) በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከሰዓት በኋላ በ10 ሰዓት እስረኞቹ ጋላባት ፓሊስ ጣቢያ ነበሩ። አሁን ማምሻውን በደረሰን ዜና መሰረት እስረኞቹ ተፈተው መተማ ከተማ መድረሳቸውና ጎንደር ላሉ ቤተሰቦቻቸው ስልክ በመደወል ላይ መሆናቸው ታውቋል።

## የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሁኔታ ፥

በሌላ በኩል ደግሞ የሱዳን ጦር በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚያካሂደውን ወረራ በተመሳሳይ መልኩ ወደ ደቡብ ምዕራብ በማስፋፋት በጋምቤላና በአካባቢ ለም ቦታዎችን በመያዝ ሕዝቡን ከትውልድ ቦታው በማፈናቀል ላይ ይገኛል።

ለኢትዮጵያ ሕዝብ ድኅንነት ከመቆም ይልቅ ለሱዳን መንግሥት ወኪል የሆነው የአቶ መለስ ዜናዊ አገዛዝ ፤ እርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትር እና የጎን ስፋቱ ከ30 እስከ 50 ኪሎ ሜትር የሆነውን የሀገራችን ለም መሬት ለሱዳን መንግሥት አሳልፎ ለመስጠት ያወጣውን እቅድ ደረጃ በደረጃ በተግባር ላይ ያዋለው መሆኑ ይህ ተጨባጭ ማስረጃ ነው።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!
የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የአባቶቻችን ቃል-ኪዳንና አደራ አለብን!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
**P. O. Box 656 • Tucker, GA 30085 USA**
**E-mail: leethiopia@yahoo.com**